*

# በዓይናችን፡አሳየን

ጎዋ ድረስ ያመጠቀን ጥዑመ ዜማ ቅኝት
ድንበሩን ጥሶ ያለፈ የማይታዘዝ ለምድር ስበት
በስሜት ተውጦ አካልህ ሲፈነዳ ተመንጭቆ
ልሳንህ በኛ ላይ ገዝፎ ስነልቦናችን ተሰርቆ
ሲታደስ በዜማህ ነፍሳችን ሲርመሰመስ በደማችን
የፈቃድ ሞት እየሞትን በመድረክ ድል ተደርገን

ተቃኝቶ ተቀናብሮ መሳሪያው ሲያስተጋባ
እንደ፡አውሎነፋስ ተሽከርክሮ በጆሮአችን ሲገባ
ጣዕመ ዜማህ ሲንቆረቆር ቆልምመህ ስትንሳፈፍ
ከመስማት አልፎ አየነው ህይወት አግኝቶ ሲከንፍ
ምህተዓመት የሰው ልጅ ዜማን ሲሰማ ቆይቶ
እንድናይ አረገን ማይክል በአካሉ፡ኖታውን ሰርቶ

ፀሓይ ግለትዋን አውሳህ አዝጋሚ ጉዞን ጨረቃ
በማይታመን ተሰጣኦ መሬት አንተን፡አድንቃ
እያየ ኪነ ተአምር ፍጡር ተወልዶ ሲከስም
እየመሸ እየነጋ እስከወዲያኛው ዝንተዓለም
ፈቃድዋ እስካለ ምድር በሰው መኖሪያነትዋ
የማይደገም አቀንቃኝ ማይክል ይሆናል እንደበትዋ

ነፍስህ ጸጋን ትታደል የማያልቀውን የገነት
የአቢሲኒያ ምርኮኞችህ ያስታውሱሃል በጸሎት
ለጋሽ ጥላሁን አድርሰልን የከበረውን ሰላምታ
ከኛ ጋር አብሮ አለ በህለት ተለት ትውስታ

ብርዞ ለሚይክል መታሰቢያ